ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
Re'ese Adbarat Debre Selam Kidest Mariam
Ethiopian Orthodox Tewahido Church
"እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀመዝሙር አድርጓቸው።" ማቴ ፳፰፥ ፲፱
"Therefore go and make disciples of all nations, baptizing them in the name of the Father and of the Son and of the Holy Spirit, " Matthew 28:19

# የባለአደራዎች ቦርድ ጽ/ቤት /OFFICE OF THE BOARD OF TRUSTEES

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::
In the name of the Father, the Son, and the Holy Spirit, Amen

## ዋሽንግተን ዲሲ

## ከባለአደራዎች ቦርድ የተሰጠ መግለጫ

## "የደከሙትን እጆች አበርቱ፥ የላሉትንም ጉልበቶች አጽኑ።"ኢሳያስ 35፡3

የርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረችበት እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከ1987 ዓም ጀምሮ፤ ላለፉት 27 ዓመታት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ተቀብላ ያቆየችውን ሥርዓተ አምልኮትና ትምህረተ ሃይማኖትን መመሪያ በማድረግ፤ በሰሜን አሜሪካ በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ምዕመናን የአምልኮተ እግዚአብሔር መግለጫ የሆነውን መንፈሳዊ አገልግሎት በጥራትና በስፋት በመስጠት መንፈሳዊና ወገናዊ ግዴታዋን ስትወጣ ቆይታለች። እንዲሁም እንደ ኤሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1954 ዓም በወጣው የአሜሪካን የፌዴራል ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው፣ የ501(C)(3) አትራፊ ላልሆኑ ማህበራት የሚሰጠውን ፈቃድ አግኝታ መንፈሳዊ፤ ባሕላዊና ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት ማህበረሰቡን ላለፉት 27 ዓመታት በማገልገል በመቅረዝ ላይ እንደምታበራ መብራት ለብዙዎች ተስፋ የሆነች ታላቅ ደብር መሆንዋ የሚታወቅ ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ የመከፋፈል ችግር ሲከሰት "ወሂአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በማለት በአንድነቷ ፀንታ እንድትኖር በማሳሰብ ለሁለት መከፈሏን የተቃወመች ግንባር ቀደም ሆና የአገር ውስጥና የውጭ ሲኖዶስ የሚለው መከፋፈል ጠንቁ አደገኛ እንደሆነ በመግለጽ ሰላምና አንድነት እንዲመሠረት በአጽንኦት ለሚመለከተው ሁሉ በወቅቱ ያሰታወቀችና የሚጠበቅባትን ተጋድሎ ያደረገች ቤተ ክርስቲያን ነች።

ላለፉት 27 ዓመታት ብዙ መስዋዕትነት በመክፈል ተቋማዊ ጥንካሬዋን፣ አደረጃጀቷን አጠንክራ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ስታበረክት የነበረችውን ብርሃኗን አጨልመው፤ ትልቅ ራዕይ ሰንቃ አዲስ ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ልትገናባ የተዘጋጀችውን ተስፋዋን ደርምሰው፤ ታዳጊ ህፃናትን በሃይማኖትና በኢትዮጵያዊነት ለማነጽ የጀመረችውን ገንቢ ዓላማ በማደናቀፍ በላፉት 3 ወራት በዶር አክሊሉ ሀብቴ የሚመራ ቡድን በአውደምህረቱ ላይ ከ8/30/2015 ጀምሮ ለ4 እሁዶች በተቀሰቀስ ሁከትና እረብሻ በቤተ ክርስቲያኗ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በምዕመናንና በካህናት የተመረጠውን የባለአደራዎች ቦርድ አፍርሰናል፤ የመተዳደሪያ ደንቡም ተሽሯል፤ በማለት ያወጁት የሥርዓተ አልበኝነት አዋጅ መነሻ ምክንያት የባለአደራዎች ቦርድ የሰውና የንብረት ደህንነት ለመጠበቅ ለጊዜው የዘጋውን የቤተ ክርስቲያን በር ሰብረው በመግባት ቤተ ክርስቲያኗ በሥርዓተ አልበኝነት በቁጥጥራቸው በማድረግ አባላት እንዳይገቡ እያደረጉ መሆናቸው የሚታወቅ ነው።

በዚህ ባለንበት አገር እንዲህ ዓይነት ሥርዓተ አልበኝነት ሲፈጸም ለማመን የሚያስቸግር ክስተት በተለይ በዕድሜ ባለጸጋና ምሁር፣ የሃይማኖት አባቶች በሚባሉ ካህናትና ሽማግሌዎች መፈጸሙ ለብዙዎቻችን ግራ ያጋባ ቢሆንም አንዳንዴ ዕድሜ አስተማሪ የሚሆነውና ያህል ሌላ ጊዜ ደግሞ አደናጋሪ መሆኑን ያረጋገጥንበት ገጠመኝ ነው።

የባለአደራዎች ቦርድም የተሰጠውን አደራ ለመጠበቅ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ አስፈላጊውን ሁሉ እያደረገ ይገኛል። እውነት ትመነምናለች እንጂ አትሞትምና የፍርድ ሂደት ጊዜ ሊወስድ ቢችልም እውነቱን ሲያረጋግጥ ትክክለኛውን ፍርድ እንደሚሰጥ እናምናለን።

የተወሰደው የቦርድ ግልበጣ ተከትሎ ማቆሚያ በሌለው ውሸት፣ አሉባላት፣ሥርዓት አልበኝነት፣ እና ኢ-ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባሮች በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ተንሰራፍቷል፡፡ ማን አለብኝ ባይነት ከላይ እስከ ታች እንዲዳረስ ሆኗል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ በውጭም ሆነ በውስጥ ለተሰለፉባት ጠላቶች የተመቸች እንድትሆን ሆናለች፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ የባለአደራዎች ቦርድ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ከመረጠው ማህበረ ምዕማንን ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በ DECEMBER 6/2015 በጠራው ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ተገናኝቶ ነበር። አባላቱ ምንም እንኳን በሥርዓተ አልበኞቹ በኩል ወደ ስብሰባው እንዳሄዱ የተካሄደባቸውን ከፍተኛ ቅስቀሳ ተቋቁመው ሰለ ቤተ ክርስቲያኔ ያገባኛል በማለት 41% በመቶ በላይ አባላት በመገኘት ጉባኤውን እውን አድርጎታል። በዚህ አጋጣሚ የቤተክርስቲያኗን አባላት ላደረጉት ቁርጠኛ ውሳኔ የባለአደራዎች ቦርድ ከልብ ያመሰግናል።

የባለአደራዎች ቦርድ በመጀመሪያ ያደረገው ጉባኤውን ለመጀመር በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ግዴታቸውን ካሟሉት 467 አባላት መካከል 1/3 መገኘታቸውን ማረጋገጥ ነበረ። ከ41% በላይ መገኘታቸውን ከተረጋገጠ በኃላ ከእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት በኋላ የዕለቱን ጸሎትና የመንፈሳዊ መልዕክት በአባታችን በርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ በሊቀማዕምራን ቀሲስ ዶር አማረ ካሣዬ ተሰጥቷል።

ጉባኤው ከባለአደራዎች ቦርድ የቀረበለትን ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ ቤተ ክርስቲያኗ ስለደረሳባት አሳዛኝ ፈተና በሰፊው ተወያይቷል። በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የደረሰው ፈተና በሀገራችን በኢትዮጵያና በዋናዋ እናት ቤተክርስቲያናችንና በሃይማኖታችን ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለው መከራና ፈተና አካል መሆኑ ተገልጿል። ይህን የደረሰብንን በደል፣ክህደትና ፈተና በጽናት ከእግዚአብሔር ጋር መታገል ይኖርብናል በማለት ጉባኤው ቃልኪዳኑን አድሷል። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን የክርስትናና የመስቀል ጉዞም በፈተና ተፈትኖ ማለፍ እናዳለበት ተማምኗል።

መንፈስንና ልብን የሚነኩ አስተያየቶች፣ መቆርቆርና ቁጭት የተቀላቀለበት ንግግሮች በእናቶችና በተለያዩ አባሎች ተደርገዋል። ጉባኤው ጥልቅ በሆኑ የቤተክርስቲያኗ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ከአደረገ በኋላ የ2016 የባለአደራዎችን ቦርድ የሚያስመርጠውን የአስመራጭ ኮሚቴ መምረጥንና በሚከተሉት ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎች አጸድቀዋል። አስተላልፏል።

1. የቤተክርስቲያኗ ሕጋዊ የባለአደራዎች ቦርድ (“ቦርድ”) አባላት በ September 1, 2015 ዓም እና አሁንም ድረስ የሚከተሉት ግለሰቦች መሆናቸውን አባላቱ አረጋግጧል።
    1. ዶ/ር አማረ ካሣዬ፥ አስተዳዳሪ;
    2. ዶ/ር ጌታቸው መታፈሪያ፥ ሊቀመንበር;
    3. አቶ ሽመልስ አረጋ፥ ምክትል ሊቀመንበር;
    4. ወ/ሮ ወሰንየለዝ ደበላ፥ ጸሐፊ;
    5. አቶ መላኩ ሚሼል፥ ገንዘብ ጉዳዮች ኃላፊ;
    6. አቶ ለገሥ ተሰማ፥ አባል;
    7. አቶ ፍሬሕይወት በቀለ፥ አባል;
    8. ወ/ት ትጓደድ ከበደ፥ አባል;
    9. አቶ ይዝራው ጽጌ፥ አባል

10. አቶ ከሃሊ ወንዳፈራው ጠንፌ፥ አባል;
11. ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ሀይሌ፥ አባል;
12. ቄስ ሀይሉ ዘለቀ ልቡ፥ አባል;
13. አቶ መንገሻ አቻምየለህ፥ አባል።

እኛ አባላቱ የእነኝህን የቦርድ አባላት በሕጋዊ መመረጣቸውን ለማረጋገጥ ወስነናልና በዚህ ውሳኔ መሰረት እናረጋግጣለን። በተጨማሪም እነኝህ የቦርድ አባላት የተመረጡበትን የምርጫ ሕግ፣ በ 1996 ዓም ሆነ በ 2012 ዓም መተዳደሪያ ደንብ፥ በሕጋዊ ምርጫ የተመረጡ መሆናቸውን እናረጋግጣለን: አመራረጣቸውንም በዚህ ውሳኔ እናጸድቃለን።

2. በ October 2, 2015 በቤተክርስቲያኗ ከሳሽነት የቀረበው የክስ ቁ: 2015 CA 7574 ("ክሱ") ላይ ተከሳሾች ተብለው የተዘረዘሩት ("ተከሳሾች") በቤተክርስቲያኗ አገልግሎት ላይ ያደረሱትን ሁከትና ረብሻ እናወግዛለን። እነዚህ የረብሻ ድርጊቶች የተጀመሩት በSeptember 1, 2015 አካባቢ ሲሆን: አሁንም እንደቀጠሉ ነው። የእነኝህን ተከሳሾች ድርጊቶች ለማስቆም አስፈላጊ መስሎ የሚታያቸውን እርምጃዎች ቦርዱ እንዲወስድ በዚህ ውሳኔ መሰረት ወስነናል።

3. በዶ/ር አክሊሉ ሀብቴ መሪነት የሚመራውንና እራሳቸውን "የተቆርቋሪ" አባላት ኮሚቴ ብለው የሰየሙትን ግለሰቦች አመራር እንደማንቀበል እኛ አባላቱ ወስነናል። ይህ ኮሚቴ በአግባቡ ያልተመረጠና ከአባላቱ ፈቃድ ያላገኘ በመሆኑ: የእነኝህን ግለሰቦች ድርጊት ለማስቆም ቦርዱ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ወስነናል።

4. የቤተክርስቲያናችን አስተዳዳሪ ከቤተክርስቲያኗ ቅጥር ግቢ አለአግባብ መባረራቸውንና መታገዳቸውን እናወግዛለን። እንዲሁም ተከሳሾችና ግብረአበሮቻቸው ካለፈቃድ ቤተክርስቲያኗን በቁጥጥራቸው ማዋላቸውን እናወግዛለን። ቦርዱ አስተዳዳሪውን ወደ ቦታቸውና ሥራቸው ለመመለስ: እንዲሁም ቤተክርስቲያኗንና ግቢዋን ከተከሳሾች ቁጥጥር ለማውጣት አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ እንዲወስድ ወስነናል። እስካሁንም ድረስ ቦርዱ የወሰዳቸውን እርምጃ በሙሉ አጽድቀናል።

5. እኛ አባላቶቹ የቤተክርስቲያኗን ግቢ ከSeptember 25, 2015 ጀምሮ በቁጥጥራቸው ያዋሏትን ተከሳሾችንና ግብረአበሮቻቸውን እናወግዛለን። ይህም ድርጊታቸው ሕገወጥና ያለአባላቱ ፈቃድ መሆኑን እንዲሁም የአባላቱን ፍላጎት የሚጻረር መሆኑን እንገልጻለን። እነዚህን ሰዎች ከቤተክርስቲያኗ ግቢ ለማስወጣት ወደፊትም ለማገድ አስፈላጊው የሕግ እርምጃ እንዲወሰድና ክስ እንዲጀመር ወስነናል። ይህንንም ለማድረግ ለጠበቃ ለመቅጠርና ሌላም አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ አስፈላጊው ወጪ በሙሉ እንዲደረግ ወስነናል። ይህንንም በሚመለከት ቦርዱ የፈጸማቸውን ድርጊቶች በሙሉ እነሆ አጽድቀናል።

6. እኛ አባላቱ ከተከሳሾቹ ጋራ ቅራኔ እንዳለን እያረጋገጥን ተከሳሾቹንና ግብረአበሮቻቸውን ከቤተክርስቲያኗ ግቢ ለማስወጣትና ካለቦርዱ ፈቃደ ቤተክርስቲያኗ ቅጥር ግቢ እንዳይገቡና እንዲታገዱ ቦርዱ እስካሁን ድረስ የወሰዳቸውን እርምጃዎችን በሙሉ በዚህ ውሳኔ አጽድቀናል። እነዚህም እርምጃዎች በቤተክርስቲያኗ ስም የሕግ አማካሪ ጠበቃዎች መቅጠሩንና፥ ክስ መጀመሩን: በተለይ የማገጃ ክስና ጊዜያዊ ማገጃ ትዕዛዝ ማመልከቻ ያመለከተውን እንዲሁም ሌሎችን የወሰዳቸውን እርምጃዎችን ይጨምራል። በተለይም ቦርዱ ክሱን መመስረቱንና ለዚህም ክስ ያወጣውን ወጪ በሙሉ አጽድቀናል።

7. በ2012 ዓም፣2014 ዓም እና 2015 ዓም የተካሄዱት የአጠቃላይ አባላት ጉባኤዎች በሥነ ሥርዓትም ሆነ በይዘታቸው ጉድለት ካለባቸው፤ እኛ አባላቱ በዚህ ውሳኔ መሠረት እነኝህን ስብሰባዎችና፤ በእነኝህም ስብሰባዎች የተላለፉትን ውሳኔዎችንና የተወሰዱትን እርምጃዎች በሙሉ አጽድቀናል። በእነኝህ በ2012፤ 2014፤ እና በ2015 የአባላት ስብሰባዎች ላይ የተወሰኑት ውሳኔዎች ሁሉ፤ የተሰጡ ማሳሰቢያዎች እና የተወሰዱት እርምጃዎች ሁሉ፤ ሙሉ ኃይልና ሥልጣን እንዲሰጣቸው ወስነናል።

8. እኛ አባላቶች በ November 2015 አባላት ነን በሚሉ ግለሰቦች ተካሄደ የተባለውን የቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ የአባላት ጉባኤ አናውቀውም ላለመቀበልም በዚህ ውሳኔ መሠረት ወስነናል። ስለዚህ ስብሰባ መካሄድ ከአብዛኛው አባላት በላይ ማስታወቂያም ሆነ የጥሪ ደብዳቤ ያልደረሰው በመሆኑ ምክንያት ይህ ስብሰባ ሕገወጥና ትክክለኛ ያልሆነ ነው ብለን ወስነናል። በዚህ ስብሰባ ላይ የተወሰኑት ውሳኔዎች በሙሉ የአባላቱንና የቤተክርስቲያኗን ፍላጎት የማያንጸባርቁ መሆኑ እንዲያውም የአባላቱንም ሆነ የቤተክርስቲያኗን ፍላጎት የሚጻረሩ መሆናቸውን ተስማምተን ወስነናል።

9. ቦርዱ የቤተክርስቲያኗን ገንዘብ ለመጠበቅ ሲል አዲስ የባንክ አካውንት ከፍቶ ከነባር አካውንቱ የተወሰነውን ገንዘብ አውጥቶ በአዲሱ አካውንት በመጨመር የወሰደውን እርምጃ እኛ አባላቱ በዚህ ውሳኔ አጽድቀናል።

10. በተከሳሾቹና ግብረአበሮቻቸው ድርጊቶች የተነሳ የደረሰውን ችግር ለመቀነስ እኛ አባላቱ ወስነናል። ስለዚህም ለ2016 የታቀደውን የቦርድ ምርጫ ሳይውል ሳያድር እንዲካሄድ ወስነናል። በመሆኑም የአገልግሎት ዘመናቸው ያበቃውን የቦርድ አባላት ለመተካት በ2016 የሚካሄደውን የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባንና ምርጫ እንዲመሩ ስማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘረው አባላት በአስመራጭ ኮሚቴ እንዲያገለግሉ ወስነናል።

1. ግሪጎሪ በራዩር (Gregory Brauer)
2. ዮሃንስ ሙላት
3. አልማዝ ሳህሌ
4. ግርማ ተሰማ
5. ሰለሞን ታፈሰ
6. ወይንሸት ከበደ
7. የሺ መንግሥቱ

11. እስከ ዛሬ ድረስ፡ በተለይም ከ1996 ዓም ወዲህ የቦርድ አባላትን ለመምረጥ ምርጫ ላይ ድምጽ መስጠት የሚችለው አባል ልክ ከምርጫው በፊት በነበሩት 6 ወራት የአባልነት ክፍያውን ሳያቋርጥ የከፈለ ብቻ ነው። ይህ አንዱና ዋንኛው መስፈርት ነው። በእንዲህ አይነት ሲንሠራ ቢያንስ 20 ዓመት ሆኖናል። አሁንም በ 2016 ዓም በሚካሄደው ስብሰባ ይህ መመዘኛ እንደተጠበቀ እንዲሆን ወስነናል።

12. ተከሳሾቹና፣ ግብረአበሮቻቸው አባላትንና ማንኛውን የቤተክርስቲያኗን አባል ከቤተክርስቲያኗ ግቢ ማገዳቸውንና በቅዳሴ እንዳይሳተፉ ማድረጋቸውን እናወግዛለን። እንዲሁም አምባጓሮ መፍጠራቸውና ከቤተክርስቲያኗ ተልክኦና ዓላማ ጋራ የሚጻረር ሁኔታዎችን መፍጠራቸውን እናወግዛለን። በዚህ ድርጊታቸው የተነሳ ተከሳሾችና የቤተክርስቲያኗ አባላት የሆኑ ግብረአበሮቻቸው ከአባልነት እንዲታገዱ ወስነናል፤ በዚህም ውሳኔ መሠረት አግደናቸዋል።

13. የቦርዱ አባላት የሆኑ ተከሳሾች ቀሲስ ኃይሉ ዘለቀና መንገሻ አቻሜለህ ከቦርድ ሥልጣናቸው መነሳት እንደሚገባቸው እኛ አባላቶቹ ወስነናል። በመሆኑም ቦርዱ እነኝህን የቦርድ አባላት የሆኑትን ተከሳሾች ከቦርድ ሥልጣናቸው እንዲነሱ እናሳስባለን። እንዲሁም ሊቀሊቃውንት ወርቅነህ ኃይሌ ከቦርድ አባልነታቸው እንዲነሱ ወስነናል።

14. ቤተክርስቲያኗ በተከሳሾቹ ድርጊት የተነሳ የደረሰባትን ጉዳት በሚመለከት ረገድ ቦርዱ በተከሳሾቹና በግብረአበሮቻቸው ላይ የሕግ እርምጃ እንዲወስድባቸው እኛ አባላቶቹ ወስነናል:: በተለይ ከጉዳቶቹ አንዱ በተከሳሾቹና ግብረአበሮቻቸው የተነሳ ቤተክርስቲያኗ ከተቋራጮች ጋራ የነበራት የሕንጻ ማሠሪያ ውል በመሰረዙ ምክንያት አዲስ ውል ለመዋዋል የሥራው ዋጋ በጣም በመጨመሩ ምክንያት ትልቅ ጉዳትና ኪሣራ ደርሶባታል::

15. በቤተክርስቲያኗ ውስጥ በሚካሄደው አምባጓሮ ሰው መጎዳቱ የማይቀር ነው:: የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው:: እንዲያውም አሁንም እንኳን ጉዳት የደረሰባቸውና የተዋረዱ ግለሰቦች መኖራቸው ተረድተናል:: በተከሳሾቹና ግብረአበሮቻቸው ምክንያት ቤተክርስቲያኗ የሚደርስባት ያለው የማይቀለበስ ጉዳትን ለማቆምና የሚካሄደውን አምባጓሮ ለማቆም: ቦርዱ አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ እንዲወስድ፤ አስፈላጊ መስሎ ከታየውም ቤተክርስቲያኗ ለአገልግሎት እንድትዘጋና የእለት ተእለት የአስተዳደሩን ሥራ አስተዳዳሪው እንዲያካሂዱ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ቦርዱ እንዲያመለክት ወስነናል::

16. ተከሳሾቹና ግብረአበሮቻቸው በቤተክርስቲያኗ ሥም የሰበሰቡትን ገንዘብ በሙሉ ለቦርዱ እንዲያስረክቡ ወስነናል:: እንዲሁም በተከሳሾችና ግብረአበሮቻቸው እጅ የሚገኘውን የቤተክርስቲያኗ ንብረት በሙሉ ለቦርዱ እንዲአስረክቡ ወስነናል:: ይሄንንም ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ ቦርዱ አስፈላጊ ወይም ተገቢ የሆነውን እርምጃ እንዲወስድ ወስነናል::

17. ቦርዱ እነኝህን ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲያደርግና ለዚሁም አስፈላጊ ወይም ተገቢ የሆነውን እርምጃዎች እንዲወስድ ወስነናል::

እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ እንድንገናኘና በቤተ ክርስቲያናችን ጉዳይ ላይ አስፈላጊ በሆኑ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ወሳኔ እንድናስተላልፍና ስለረዳን ክብር ምስጋና ለአምላካችን ለመድኃኒዓለም ለእናቱ ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም እንዲሆንልን በሚል በምስጋና መዝሙርና ጸሎት የዕለቱ ጉባኤ ተፈጽሟል።

ወሰብሐት ለእግዚአብሔር
የባለአደራዎች ቦርድ

ኅዳር ፳፱ ቀን ፳፻፰ ዓም / DECEMBER 9,2015